# ***አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ለሥራ አስፈፃሚ አባላቱ የሦስት ቀናት ሥልጠና ማዘጋጀቱን አስታወቀ::***

### ***ከኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ስማችሁን ቀይሩ በአንዳንድ መተዳደሪያ ደንባችሁ ላይ ማብራሪያ ስጡ መባላቸውንም ገልፀዋል::***

የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ አባልና የእቅድና ስትራቴጂ ጉዳይ ኃላፊ አቶ አክሉ ግርግሬ ድርጅታቸው ሥልጠናውን በሦስት የተለያዩ ርእሶች ላይ እንዳዘጋጀና የፊታችን አርብ እንደሚጀምር ገልፀዋል:: እስካሁን የሚደረግበትን ቦታ እንዳልወሰኑ የሚናገሩት አቶ አኪሉ የሥልጠናው ርእሶችና ዝግጅቱ ግን ተጠናቋል ብለዋለል::

እንደ አቶ አክሉ ገለፃ የሥልጠና ፕሮግራሙ የተዘጋጀባቸው ርእሶች የግጭት አፈታት (Conflict Management) ፣የቡድን ምስረታና ግንባታ (Group Dynamics)፣ እና እቅድ አዘገጃጀት(Program Planning) ናቸው:: የሥልጠናው ዓላማ አባላቱ እስካሁን ያለፉባቸውን ሂደቶች ዞረው እንዲያዩና እንዲማሩበት፣ ለወደፊቱ እንዴት መቀጠል እንዳለባቸው ልምድ የሚቀስሙበት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል::

በየ15 ቀኑ የሥራ አስፈፃሚ አባላቱ እየተገናኙ ይወያያሉ የሚሉት አቶ አኪሉ ይህ ሥልጠና ልዩነቶቻችንን የምንፈታበትን መንገድና ቁልፍ መርሆ ይዘን እንወጣበታለን ብለን እንጠብቃለን ብለዋል:: ሥልጠናውን አንድ ብለን ጀመርነው እንጂ በተከታታይ የሚደረግና እንደአስፈላጊነቱ እስከ ተራ አባላት ሊወርድ ይችላል ያሉት አቶ አክሉ የስልጠናውን ሠላማዊነት እና ቀጣይነት ለማብሰር ስያሜውን «አሻም» ብለነዋል ይላሉ:: አሻም ረጅም ጉዞ የሚሄድን፣ ከባድ ሥራ የሚሠራን ስው ለማበረታት የሚባል የቆየ ሀገርኛ አባባል ነው:: ከአቶ አክሉ ገለፃ ለመረዳት እንደተቻለው ቀጣይ ሥልጠናዎች በአመራር ሰጪነት(Leadership)፣ በመልካም አስተዳደር(Good Governance) እና በመሳሰሉት ርእሶች ላይ ይዘጋጃል:: የፊታችን አርብ የሚጀመረውን ሥልጠና ዶ/ር ታደሰ ብሩ እንደሚሰጡት ታውቋል::

በሌላ ዜና፤ አንድነት ስሙን እንዲቀይር ሕገ ደንቡን እንዲያሻሽል ከምርጫ ቦርድ ታዟል ስለመባሉ የጠየቅናቸው አቶ አክሉ « ምርጫ ቦርድ አንድነት የሰው ስም ነው በሚል መጠቀም አትችሉም፣ የሕገ ደንባችሁን የተወሰኑ ሀረጋት ላይ ማብራሪያ ስጡኝ ብሎ በደብባቤ ጠያቆናል:: እስካሁን ከነጭራሹ ስሙን መጠቀም አትችሉም አልተባልንም በውይይት ልንፈታው እንችላለን » ሲሉ መልስ ሰጥተዋል:: ስሙን ከነጭራሹ ቢከለከሉ ያዘጋጁት አማራጭ ይኖር እንደሆን ለጠየቅናቸውም ሲመልሱ እስካሁን ስማችንን እናጣለን የሚል እምነት የለንም፣ አትጠቀሙ ከተባልን ግን አባላቶቻችንና ብሔራዊ ምክር ቤቱ ተወያይቶ የሚወስንበት ይሆናል ብለዋል::

በዚሁ ጉዳይ ላይ ፤ በሀገር ቤት ቅዳሜና ዕሁድ ታትመው በሚወጡት ጋዜጦች ላይ፤ ተጠይቀው ያብራሩት የህዝብ ግንኙነት ሀላፊው ዶ/ር ኃይሉ አርአያ «አንድነት» በሚለው አጭር ስም ብቻ መጠቀም አትችሉም፣ በሙሉ ስሙ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፤ ነው መጠቀም የሚገባችሁ ነው ምርጫ ቦርድ ያለው ብለዋል:: አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በፓርቲነት ለመመሥረት የሚያስችለውን ሂደት የጀመረው ከአንድ ወር በፊት ሲሆን በጊዜው ፖሊስ ለስብሰባው ፈቃድ አላወጣችሁም ብሎ የምስረታና የጠቅላላ ጉባኤውን መበተኑ አይዘነጋም:: በዚሁ ምክንያት ፓርቲው ከጥቂት ቀናት በኋላ፤ የመመስረቻ ጠቅላላ ጉባዔውን በጽህፈት ቤቱ ውስጥ ማካሄዱ የሚዘነጋ አይደለም::